ከንቲባ ፅህፈት ቤት
አዲስ አበባ,ኢትዮጵያ

Office of the Mayor
Addis Ababa,Ethiopia

ከንቲባ ፅህፈት ቤት-አዲስ አበባ
-Office of the Mayor-
Addis Ababa,Ethiopia

ቀን 25/01/14
Date
ቁጥር ፅ/ከ/ፅ03/30.10/1
Ref.No

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ለአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ኮሚሽን
አዲስ አበባ፣

ጉዳዩ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ 17ኛ መደበኛ ስብሰባ የተወሰኑ ውሣኔዎችን ስለመላክ፣

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ነሐሴ 18 ቀን 2013 ዓ.ም. ባካሄደው በ17ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ከተወሰኑ ውሣኔዎች ውስጥ አጀንዳ ቁጥር 3 በተቋማችሁ አማካኝነት የሚፈፀም በመሆኑ የቃለ ጉባኤውን ኮፒ 19 ገፅ ከዚህ መሸኛ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እያሳወቅን በዚሁ መሠረት ተግባራዊ እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ//
ለምክትል ከንቲባ
ለከንቲባ ጽ/ቤት
ለከንቲባ ጽ/ቤትና የካቢኔ ጉዳዮች ዘርፍ ም/ኃላፊ
አዲስ አበባ፣

office +251-55 01 11- fax:-011 11 55 36 88
Posta Code 365,2445
Office of the Mayor
Addis Ababa,Ethiopia

4. ይህ ደንብ ወደ አፈጻጸም በሚገባበት ጊዜ የሚያጋጥሙ ችግሮች አደረጃጀቱ እየታየ የሚሻሻል ሆኖ በሚወጣው የማስፈጸሚያ መመሪያ መሰረት የሚያጋጥሙ ችግሮች እየተፈቱ የሚሄዱ መሆናቸውን ታሳቢ ተደርጎ ወደ ተግባር እንዲገባ በማለት በሙሉ ድምፅ ፀድቋል፡፡

**አጀንዳ ቁጥር 3፡-<u>የከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ በጥር 02/2013 ዓ.ም በ6ኛ መደበኛ ስብሰባው ላይ ያጸደቀው የአርሶ አደር ይዞታዎች መብት ፈጠራ መመሪያ ማሻሻያ ላይ ውይይት በማድረግ ውሳኔ ማሳረፍ፤</u>**

ለአርሶ አደሩ የመሬት ባለቤትነት መብት ለመፍጠር አርሶ አደሩ አለኝ የሚለውን መረጃ ሲያቀርብ የቀረበው የመብት ፈጠራ ጥያቄ ከአካባቢው በሚመረጡ ኮሚቴዎች የሚቀርቡ መረጃዎች ተጣርተው ለባለመሬቱ የመብት ፈጠራ ስራ እንዲሰራ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጥር 02/2013 ዓ.ም በ6ኛ መደበኛ ስበሰባው ውሳኔ ማሳለፉ ይታወሳል፡፡ በዚህም መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደር የመኖሪያ ቤትና የከተማ ግብርና መጠቀሚያ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ እና ዘላቂ የልማት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የወጣ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 20/2013 ማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 1/2013 የከተማው ካቢኔ መመሪያውን በማስፈጸም ረገድ በተግባር የታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ በመመሪያው አንቀጽ 21 መሠረት ይህንን የማሻሻያ ሃሳብ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

**አጭር ርዕስ** ይህ መመሪያ "የአርሶ አደር የመኖሪያ ቤትና የከተማ ግብርና መጠቀሚያ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ እና ዘላቂ የልማት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የወጣ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 20/2013 ማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 1/2013 ዓ.ም " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ የመመሪያው ማሻሻያ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (2.9) ተሰርዞ በ “2.9 "የአርሶ አደር ልጅ" ማለት የአርሶ አደር ልጅ ስለመሆኑ ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና መረጃ ጽህፈት ቤት የተሰጠ የልደት ምስክር ወረቀት እና በቅርበት በአካባቢው ስለመኖሩና የአርሶ አደር ልጅ ስለመሆኑ አምስት በአካባቢው የሚኖሩና የነዋሪነት መታወቂያ የሚያቀርቡ ምስክሮች የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል መሆኑ ሲረጋገጥ” በሚል ተተክቷል፡፡

በመመሪያው አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (7.2.6) የሚከተለው አዲስ ንዑን አንቀጽ (7.2.7) ተጨምሮ "7.2.7 በሌሎች ሕጎች ያሉ ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ የአርሶ አደሩ ልጅ አገልግሎት ሲጠይቅ የአርሶ አደር ልጅ ስለመሆኑ በአምስት የአካባቢው ነዋሪዎች ምስክርነት ያረጋግጣል፤ ማስረጃውን ለወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ይልካል፤ የመመሪያው አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (9.5) ተሰርዞ በ“9.5 የአርሶ አደር ልጅ ለብቻው በግብርና አገልግሎት እየሰጠ ያለ መሬት ካለውና አገልግሎት ጠያቂው የአርሶ አደር ልጅ መሆኑን በአምስት የአካባቢው ነዋሪዎች ምስክርነት ሲረጋገጥ፣ የልደት ምስክር ወረቀት ሲያቀርብ ወይም ልጅ ስለመሆኑ

1.________ 2.________ 3.________ 4.________ 5.________ 6.________ 7.________ 8.________ 9.________

10.________ 11________ 12________ 13.________ 14.________ 15.________ 16.________ 17.________

18.________ 19.________ 20.________ 21________ 22.________

በፍርድ ቤት የተረጋገጠ ህጋዊ ማስረጃ ሲያቀርብ ይዞታው ተለክቶ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል" በሚል ተተክቷል፡፡

በመመሪያው አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (9.15) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 9.16 ተጨምሯል "9.16. አርሶ አደሩ በማንኛውም ጊዜ ያለ አግባብ መሬቱን ለሌላ አካል ተላልፎብኛል ብሎ ቅሬታ ለሚመለከተው አካል ሲያቀርብ እና ተጣርቶ ውሳኔ ሲሰጠው ቀደም ሲል በአርሶ አደር መሬት ላይ የተሰራው ካርታ መክኖ መሬቱ ለአርሶ አደሩ ይመለስለታል፤ "9.17. በአርሶ አደሩ ይዞታ ላይ በማንኛውም ጊዜ ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ ለሌላ ሶስተኛ ወገን መተላለፉ በጥቆማ ወይም በማንኛውም ሌላ መንገድ በዚህ መመሪያ መሰረት ከተረጋገጠ የይዞታ ካርታው መክኖ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ይደረጋል፡፡ በጥፋቱም አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡" በማለት የዐቃቤ ሕግ የመመሪያ ማሻሻያ ሃሳብ ለካቢኔ አቅርቧል ፡፡

የካቢኔ አባላት በከተማ አስተዳደሩ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ የመመሪያ ማሻሻያ ሃሳብ ላይ አስተያየትና ጥያቄ እንዲቀርብ ክብርት ም/ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ ጋብዘው ከካቢኔ አባላት ለተነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች የዐቃቤ ሕግ ቢሮ ም/ ኃላፊ አቶ አሰፋ መብራቴ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

**የካቢኔ ውሳኔ፡-**

ካቢኔው በዐቃቤ ሕግ ቢሮ የአርሶ አደር የመኖሪያ ቤትና የከተማ ግብርና መጠቀሚያ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ እና ዘላቂ የልማት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የወጣ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 20/2013 ማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 1/2013 የአፈጻጸም መመሪያ ማሻሻያ ሃሳብ በመቀበል ተግባራዊ እንዲደረግ እና በማንኛውም ሰዓት ከአርሶ አደር መሬት ጋር በተያያዘ በሕገወጥ መንገድ የተያዘ መሬት ስለመኖሩ ጥቆማ ሲቀርብና ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ መሰረት አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በማለት በእለቱ በተገኙ የካቢኔ አባላት በሙሉ ድምፅ ፀድቋል፡፡